# የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
# የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የውስጥ መመሪያ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሥራን የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች ለመተግበር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 51/2010 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 እና 9 ላይ የተቀመጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ይህን የውስጥ  መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የውስጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የውስጥ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሸሻለው)፣ በፌዴራል መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"የስራ ክፍሎች" ማለት** ለህዝብ ይፋ የሚደረጉ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መረጃዎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሂደት የሚሳተፉ የሚኒስቴሩ ዳይሬክቶሬቶች ሲሆኑ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር፣ የፊሲካል ፖሊሲ፣ የታክስ ፖሊሲ፣ የትሬዠሪ፣ የመንግስት ሂሳብ፣ የእንስፔክሽን፣ የቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ፣ የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማትና ትብብር፣ የተባበሩት መንግስታት-ተቋማት የአየር ንብረት ለውጥ ፋሲሊቲ አህጉራት ኢኮኖሚ ትብብር፣ የብድር አስተዳደር፣ የመንግስታት ትብብር፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የኢትዮ-ቻይና፣  የዕቅድ፣ የፋይናንስና ግዢ አገልግሎት፣

የውስጥ ኦዲት፣ የህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን፣ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ዳይሬክቶሬቶች፣ የአይቤክስ/ኢፍሚስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሚኒስቴሩ ዳይሬክቶሬቶች ናቸው፡፡

2. "መመሪያ" ማለት የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ወሰን

ይህ የውስጥ መመሪያ በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 51/2010 መሰረት በሚኒስቴሩ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎችን በሚያዘጋጁና በሚያሰራጩ የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. የመመሪያዉ ዓላማ

የዚህ የውስጥ መመሪያ ዓላማ የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች፡-

1. የሚኒስቴሩን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን በተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት ዜጎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉበት ዘዴ፣ በወቅቱና በተሟላ መልኩ ተደራሽ እንዲያደርጉ በማድረግ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
2. የዜጎች ተሳትፎን እንዲያጎለብቱ በማድረግ የመንግስት ሀብት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና የህዝብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ናቸው ፡፡

## 6. መርሆች

የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች ማንኛውንም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ተግባር ሲያከናውኑ የሚከተሉትን መርሆች መሠረት ማድረግ አለባቸው፡-

1. የሚኒስቴሩ የመንግስት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎች ህብረተሰቡ ሊረዳው በሚችል መልኩ ተሟልቶ እና ወቅቱን ጠብቆ ተደራሽ መደረጋቸውን፣
2. የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ ወይም የተግባሩ ቀጥታ ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል በበጀት ሂደቱ በተሟላ መልኩ የሚሳተፍበት ምቹ ሁኔታ የተፈጠረለት መሆኑን፣
3. በማንኛውም የበጀት ምንጭ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት በዕቅዱ መሠረት በቁጠባ፣ በብቃት፣ በጥራት እና በውጤታማነት የተከናወኑ እንዲሁም በአፈፃፀም የሚታዩ አሉታዊ ልዩነቶች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን፣

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

**7. የሚኒስቴሩ ስራ ክፍሎች ኃላፊነትና የስራ ድርሻ**

**ለህዝብ ይፋ የሚደረጉ የፋይናንስ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መረጃዎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሂደት የሚሳተፉ የሚኒስቴሩ ስራ ክፍሎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፡-**

**1. የህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት**

ሀ. በመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ስር የተዘረዘሩትን የሚኒስቴሩን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ለአፈጻጸሙም የሚኒስቴሩን የስራ ክፍሎች ያስተባብራል፤

ለ. የመ/ቤቱን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስራን ከዕቅድ እስከ አፈጻጸም በበላይነት ያስተባብራል፤ የአፈጻጸም አጠቃላይ ሪፖርት ለሚኒስትሩና ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ያቀርባል፤

ሐ. የሚኒስቴሩን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ያዘጋጃል፤ ያስተባብራል፤

መ. በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 10 እና 13 የተዘረዘሩትን መረጃዎች ከመመሪያው ጋር በአባሪነት በተያያዙት አመላካቾች መሰረት ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ያደርጋል።

ሠ. በአጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት መሠረታዊ የበጀት መረጃዎችን እና ሌሎች የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን ከሚመለከታቸዉ ዳይሬክቶሬቶች በማሰባሰብ በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 14 መሰረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ይፋ ያደርጋል፣

ረ. ከሚኒስቴሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ አገራዊ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የአፈጻጸም መረጃዎችን እና ተሞክሮዎችን በድምጽና በምስል በመቅረጽ እና በጽሁፍ በማዘጋጀት ለዜናች ተደራሽ ያደርጋል፣

## 2. የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት

በአገር አቀፍ ደረጃ የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የማሻሻያ ፕሮጀክትን የማስተባበር፣ አፈጻጸሙን የመከታተልና የመደገፉ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚኒስቴሩ ደረጃ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

ሀ. ሚኒስቴሩ የተመደበለትን በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ያገኘውን የዕርዳታና የብድር ገንዘብ መረጃ በግልጽ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

ለ. ሚኒስቴሩ የፌዴራል መንግሥት መሠረታዊ የበጀት መረጃዎችን እና ሌሎች የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎች ለዜጎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ. ሚኒስቴሩ በተጨማሪነት የሚቀርፃቸው አዳዲስ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎች ካሉ በመገምገም ሥራ ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፣

መ. የሚኒስቴሩን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ከህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ይቀበላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

ሠ. የህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ልዩ ልዩ አገራዊ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የአፈጻጸም መረጃዎችን እና ተሞክሮዎችን በድምጽና በምስል በማዘጋጀት ለዜጎች ተደራሽ እንዲያደርግ ስራውን ያስተባብራል፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

## 3. የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ሀ. የፌዴራል መንግሥት መሠረታዊ የበጀት መረጃዎችን እና ሌሎች የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ለማድረግ ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 1.3 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. በአገር ደረጃ ከተቀመጠው የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የፕሮግራም ግብ አኳያ ባለፈው በጀት ዓመት የተደረሰበት እና በበጀት ዓመቱ ሊደረስበት የታቀደውን ውጤት፣ ግብና የግብ ስኬት መረጃ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ሐ. በአገር ደረጃ የተያዙ የፌዴራል መንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶች ዝርዝር መግለጫ መረጃዎችን ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 4.1 እና 4.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

መ. ለፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ከማዕከላዊ የመንግስት ግምጃ ቤት፣ ከብድር፣ ከዕርዳታ እና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች የተገኘ የመንግስት የትርፍ ድርሻ ገቢ ለበጀት ዓመቱ ለመደበኛና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚደረግ የበጀት ድጎማ እና ለዕዳ ክፍያ የተመደበ ጥቅል የበጀት መረጃዎችን በአባሪ 1.3 እና 1.10 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

4. **በሚኒስቴሩ የኢኮኖሚ ትብብር ዘርፍ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች**

በዘርፉ የሚገኙ የብድር አስተዳደር፣ የመንግስታት ትብብር፣ የአውሮፓ ህብረት ትብብር፣ የኢትዮ-ቻይና ልማት ትብብር፣ የተባበሩት መንግስት ተቋማት የአየር ንብረት ለውጥ ፋሲሊቲ የአህጉራት ኢኮኖሚ ትብብር እና አለም አቀፍ ፋይናንስና ተቋማት ትብብር ዳይሬክቶሬቶች የሚመለከታቸውን የፌዴራል መንግስቱ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ያገኘውን የብድር እና ዕርዳታ መረጃ በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በማዘጋጀት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፣

5. **የቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት**

ሀ. ለፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለልዩ ልዩ ድርጅቶችና ተቋማት ከማዕከላዊ የመንግስት ግምጃ ቤት፣ ከብድር፣

ከዕርዳታ እና ከመንግስት የትርፍ ድርሻ የተገኘ ገቢ ለበጀት ዓመቱ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚደረግን የበጀት ድጋፍ የተመደበ ጥቅል የበጀት መረጃዎችን ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 1.4፣ 1.5፣ 1.6፣ 1.7፣ 1.8፣ 1.9 እና 1.10 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. ኦዲት የተደረገ የተጠቃለለ ዓመታዊ የፌደራል መንግስት ቻናል አንድ ፕሮግራሞች የገቢና ወጪ ሂሳብ መረጃዎችን በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች በመለየት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ሐ. በቻናል አንድ በኩል የሚገቡ የብድርና እርዳታ ገቢዎችን፣ ለክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች በቻናል አንድ በኩል ፈሰስ የተደረገውን በጀት የሂሳብና ኦዲት ሪፖርት ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 3 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

መ. በቻናል አንድ ፕሮግራሞች የሚተገበሩ የግዥ አፈጻጸም መረጃዎች በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 3 በአባሪ 5.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

6. **የፊሲካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት**

የፌዴራል መንግሥቱን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍ ማለትም የገቢና የወጪ ዕቅድን እንዲሁም የወጪ አሸፋፈንን የሚመለከቱ መረጃ መግለጫዎችን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

7. **የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት**

ሀ. ለፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለልዩ ልዩ ድርጅቶችና ተቋማት ከማዕከላዊ የመንግስት ግምጃ ቤት ወጪ ሆኖ የተላለፈውን ክፍያ ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 1.10 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. የፌዴራል መንግስቱ በበጀት ዓመቱ ከታክስና ታክስ ነክ ካልሆኑ ገቢዎች፣ ከዕርዳታ፣ ከብድር እና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ የተሰበሰበውን ጥቅል የገቢ መረጃ በመመሪያው አባሪ 1.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

8. **የመንግስት ሂሳብ ዳይሬክቶሬት**

ሀ. ኦዲት የተደረገ የተጠቃለለ ዓመታዊ የፌዴራል መንግስት የገቢና ወጪ ሂሳብ መረጃዎችን በመንግስት ሂሳብ ማንዋል ላይ በተገለጹት ቅጾች መሠረት በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች በመለየት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. የተጠቃለለውን የየሩብ ዓመት የፌዴራል መንግስት የሂሣብ ሪፖርት በመንግስት ሂሳብ ማንዋል ላይ በተገለጹት ቅጾች መሠረት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

9. **የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት**

የፌዴራል መንግስት ኦዲት የተደረገ የተጠቃለለ ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ፣ ገቢ፣ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዥ፣ ንብረት፣ ወጪ፣ በጀት እና ኦዲት ክትትል ሂሳብ መረጃዎችን በመመሪያው አባሪ 3 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

10. **የአይቤክስ/ ኢፍሚስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት**

የፕሮጀክቱን ዝርዝር መግለጫ መረጃዎችን በመመሪያው አባሪ 4.1 እና 4.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

11. **የ ፋይናንስ እና ግዥ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

ሀ. በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሚኒስቴሩ በዓይነት ያገኘውን ዕርዳታ ሂሳብ መረጃ ከመመሪያው ጋር በተያያዘው አባሪ 1.4 ላይ በመሙላት በመመሪያው

ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ አምስት ቀናት በፊት ለዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የየሩብ ዓመት የሂሣብ ሪፖርት በመንግስት ሂሳብ ማንዋል ላይ በተገለጹት ቅጾች መሠረት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ሐ. በሚኒስቴሩ አስፈጻሚነት የሚከናወኑ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ከተጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ከተለያዩ የበጀት ምንጮች የወጣ ወጪን ዝርዝር መረጃዎችን በመመሪያው አባሪ 4.1 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ  አምስት ቀናት በፊት ለዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

መ. የሚኒስቴሩን  የግዥ አፈጻጸም መረጃዎች  በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 3 መሠረት በአባሪ 5.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

12.የዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት

ሀ. ለሚኒስቴሩ የተመደበ በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብ የተገኘ እና በመንግስት ፋይናንስ እና ግዥ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በኩል የቀረበ በዓይነት የተገኘ የዕርዳታ ሂሳብ መረጃን በማካተት በመመሪያው አባሪ 1.4 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ለ. የሚኒስቴሩን ትልልቅ ፕሮጀክቶች ዝርዝር መግለጫ መረጃዎችን በመመሪያው አባሪ 4.1 እና 4.2 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ሐ. የሚኒስቴሩን የፕሮግራሞች ውጤቶችና ግቦች ዓመታዊ የዕቅድና የየሩብ ዓመቱን የአፈጻጸም መረጃዎች በመመሪያው አባሪ 4.3 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት  ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

**13.የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት**

የሚኒስቴሩን የውስጥ ኦዲት ግኝት፣ የተጠቃለለ ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ፣ ገቢ፣ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዥ፣ ንብረት፣ ወጪ፣ በጀት እና ኦዲት ክትትል ሂሳብ መረጃዎችን በመመሪያው አባሪ 3 ላይ በመሙላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

## <u>ክፍል ሦስት</u>

**8. ለዜጐች እና ለባለድርሻ አካላት የሚገለፁ መረጃዎች**

ሚኒስቴሩ በመመሪያው አንቀጽ 13 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተመለከቱትን መሰረታዊ የመንግሥት የበጀት መረጃዎችን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት  በህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ለዜጐች እና ለባለድርሻ አካላት ይፋ ማድረግ አለበት ፡፡

**9. የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች**

የህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት በመመሪያው ክፍል 3 አንቀጽ 14 ስር የተቀመጡትን <u>የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች በመጠቀም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚሰጡ መረጃዎችን</u> ለዜጐች እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

**10. የመረጃ ማስተላለፊያ ጊዜ ሰሌዳ፤**

የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች በመመሪያው ክፍል ሦስት አንቀጽ 15 ስር ከተጠቀሱት የመረጃ ማስተላለፊያ ጊዜ ሠሌዳ 5 የስራ ቀናት በፊት በአባሪዎቹ መሰረት እንደ የስራ ክፍሉ ኃላፊነትና የስራ ድርሻ የተዘጋጁትን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን ለህዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

<u>**ልዩ ልዩ**</u>

## 11. ከተባባሪ አካላት ጋር የሚደረግ ጥምረት

1. የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ሲተገብሩ ከሌሎች የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ተግባሪ አካላት (የማህበራዊ ተጠያቂነት እና ቅሬታ ሰሚ አካላት) ጋር በጥምረት መስራት፣ መረጃ መለዋወጥና የዜጎችን ተሳትፎ ሊያሳድግ በሚያስችል ተግባራት ላይ አብሮ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በመደበኛ፣ በብድርና እርዳታ የበጀት ምንጭ የሚከናወኑ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድና የበጀት አፈጻጸም ላይ ከተጠቃሚው የህብረተሰብ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ፤ ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መወያየት ይኖርበታል፣
3. ሚኒስቴሩ በፌዴራሉ መንግስት በጀት የሚከናወኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ ከአካባቢው ህብረተሰብና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ምክክር ማድረግ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ2 እና 3 መሰረት በሚደረገው ምክክር የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር ተገቢውን መግለጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. በፌዴራሉ መንግስት በጀት የሚከናወኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ አስፈጻሚ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ጋር ከሚያደርጓቸው ውይይቶች መካከል የጎላ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን በመምረጥ የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች መሳተፍ አለባቸው፣

## <u>ክፍል አምስት</u>

### 12. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 20 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

የካቲት 15 **ቀን 2010 ዓ.ም.**

አዲስ አበባ

**አብራሃም ተከስተ (ዶ/ር)**

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**